# ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር

# ሀገር አቀፍ የባህል ሙያ ዘርፎች ዕውቅና እና የማበረታቻ ሽልማት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 473/2013

ሰኔ 2006

# በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር

# ሀገር አቀፍ የባህል ሙያ ዘርፎች ዕውቅና እና

# የማበረታቻ ሽልማት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር

# 473/2013

የባህል ኢንዱስትሪ ዘርፍ በሀገሪቱ የህዳሴ ጉዞ ላይ ምርታማና የልማት ተዋንያን ዜጎችን በማፍራት፣ ዘርፉ በሰብዓዊም ሆነ በኢኮኖሚያዊ ልማት ላይ ያለውን ሚና ከፍ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ፤

የዘርፉሙያተኞች ሙያቸውንና ክህሎቶቻቸውን በመጠቀም ባህላዊ ዕሴቶች እንዲታወቁ፣ እንዲሠራጩና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ትልቅአስተዋፅዖየከማድረጋቸውም በተጨማሪየኅብረተሰቡን መንፈሣዊ ሕይወት በማደስና በማነፅ ለሀገሩ ተቆርቋሪ፣ ለወገኖቹ አለኝታ በልማት ተግባሩም በንቃት ተሣታፊ የሚሆን ስብዕና በመቅረፅ ረገድየሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ በመሆኑ፤

የዘርፉን የልማት ተዋናዮች ማበረታታት የሀገራችንን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ብዝሃ ባህል ለመጠበቅ፣ ለማልማትና ለማስተዋወቅ የሚያስችል አቅም የሚፈጥር በመሆኑ፤

በዘርፉ የላቀ ወጤት ለሚያስመዘግቡ የፈጠራ ሰዎች አቅም በፈቀደ መጠን ቁሳዊና ሞራላዊ ማበረታቻ እንደሚያደርግ በሕገመንግስቱ አንቀፅ 91(3) የተደነገገና እና በባህል ፖሊሲው ክፍል 7(1) ቃል የተገባ በመሆኑ፤

በዘርፉ ሽልማት መስጠት የባህል ኢንዱስትሪዎች ጠቀሜታ እንዲጠናከርእና የፈጠራ ሥራዎች አድገው እንዲበራከቱ መንገድ የሚከፍት በመሆኑ፤

ሀገር አቀፍ የሽልማትሥነ-ሥርዓት በማካሄድ በኢንዱስትሪው የሚገኙ ባለሙያዎችን በማበረታታት በየሥራዎቻቸው አርዓያነታቸውን ለይቶ ዕውቅና መስጠት፣ ለበለጠ ፈጠራና ለመልካም ውጤት በማነሳሳት በጥረት ላይ የተመሠረተ የውድድር ሥሜት እንዲኖር ማድረግተገቢ በመሆኑ፤

ለሀገር አቀፍ የሽልማት አሰጣጥ የተጠና፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት መከናወን ያለበት በመሆኑ፤

የህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅቁጥር 691/2003 አንቀፅ 31

የተሠጡትን ተግባርና ኃላፊነቶች በአግባft ለመወጣት ይህንን መመሪያ አወጥቷል፡፡

# ክፍል
# አንድ

## ጠቅላላ

1) **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ ሀገር አቀፍ የባህል ሙያዘርፎች ዕውቅና እና የማበረታቻ ሽልማት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 473/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2) **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. **"የባህል ኢንዱስትሪ"**ማለትባህልነክእውቀቶችንናሀብቶችንበመጠቀምኢኮኖሚያዊጥቅማቸውከፍተኛየሆኑባህላዊየምርትውጤቶችንየሚያመርቱየትዕይንታዊ ጥበባት፣ የዕይታዊ ጥበባት፣ የዕደ-ጥበባት እንዲሁም የሥነ-ፅሁፍ ጥበባት ኢንዱስትሪ ዘርፎችሲሆኑመሠረታቸውምባህላዊእውቀቶችናስነጥበባዊፈጠራዎችናቸው፡፡
2. **"ትዕይንታዊ ጥበባት"**ማለት ሙዚቃ፣ፊልም፣ትአትር፣ ውዝዋዜ፣ተውኔት በዘርፉ ተካተዉበት የሚገኙበት የሰዉ ልጅ ደስታውን፣ ሀዘኑን፣ ተስፋና ምኞቱነየሚያሳይበት የባህል ኢንዱስትሪ ዘርፍ ነው፡፡
3. **"ዕይታዊ ጥበባት"** ማለትሥዕል፣ፎቶግራፍ፣ሥነህንፃ፣ፋሽንእና ቅርጻ ቅርጽን ያካተተ የባህል ኢንዱስትሪ ዘርፍ ነው፡፡
4. **"ዕደ-ጥበብ"** ማለት በእጅ ውበት አላብሶ የሚያመርታቸዉ የሸማ፣ የቀርክሃ፣ የቀንድ፣ የእንጨት፣ የአንጠረኛ፣ የቆዳ፣ የቅርጫት እና መሰል ስራዎች የሚያጠቃልል የባህል ኢንዱስትሪ ዘርፍ ነው፡፡
5. **"የሥነ-ፅሁፍ"** ማለትድርሰት፣ልብወለድ፣ግጥም፣ሥነቃልያካተተ የባህል ኢንዱስትሪ ዘርፍ ነው፡፡
6. **"ዘርፍ"** ማለት የባህል ኢንዱስትሪ ዘርፍ ነው፡፡
7. **"ሽልማት"** ማለት በባህል ኢንዱስትሪው ዘርፍ ያሉትን ሙያ እና ሙያተኞች ለማሳደግ ለዘርፉ ተዋንያን የሚሰጥ ዕውቅና እና ማበረታቻ ነው፡፡
8. **"ሥራ"** ማለት በባህል ኢንዱስትሪው የሚሠሩ የእደጥበብና የጥበብ ስራዎችን ያመለክታል፡፡
9. **"የባህል ባለሙያ"** ማለት ባህልን መሠረት አድርጎበባህል ኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚሠራ ነው፡፡

10. **"ማህበራት"** ማለት በባህል ኢንዱስትሪ ዘርፍ ተደራጅተው ህጋዊ ሰውነት የተሰጣቸው አካላት ናቸው፡፡

11.**"ክልል"**ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47 የተመለከቱትን ክልሎችና አዲስ አበባንና የድሬደዋ መስተዳድርን ይጨምራል፡፡

12.**"ሚኒስቴር"** ማለት የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ነው፡፡

13.**"ዓብይ ኮሚቴ"** ማለት በዚህ መመሪያ መሠረት የሚቋቋመውኮሚቴ ነው፡፡ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

## 3) ዓላማ

የሽልማቱ ዓላማዎችየሚከተሉት ናቸው::

1. ለባህል ሙያተኞች ሁለንተናዊ የሙያ ጥበብና ለተግባራቸውም ዕውቅና ድጋፍ በመስጠት፣ ለሀገሪቱ የባህል ኢንዱስትሪ ማደግና ለሀገር ልማት የሚኖራቸውን ሚና ማሳደግ ፡፡
2. በተሸላሚዎች አርአያነት የሙያውንሥነምግባር የጠበቁ ጠንካራና የተሻሉ ተተኪዎችን ማፍራት፣
3. በዘርፉ የቀረft ምርጥ ሥራዎችን በስፋት ኢንዲተዋወቁ ማድረግ፣
4. በፈጠራ ሥራዎቻቸውና በክህሎታቸው አርአያ ለሆኑ የባህል ኢንዱስትሪዉ ተዋንያን ዕውቅናለመስጠት፣

## 4) የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በሀገሪቱ ውስጥ በባህል ኢንዱስትሪ ዘርፍ ለተሰማሩ ሙያተኞች፣ ሙያዎች እና ተቋማት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

# ስለሽልማት

## 5) የሽልማት መርሆች

1. የባህል ሙያተኞች ለሽልማት የሚቀርftት በመልካም ሥራቸው ለሌሎች አርአያ መሆን መቻላቸው ሲረጋገጥ ይሆናል፡፡

2. ለሽልማት የሚቀርft ሥራዎችየሀገራችንን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ብዝሃ ባህል ለመጠበቅ ለማልማትና ለማስተዋወቅ የሚያስችል አቅም ያላቸው ሊሆኑ ይገባል፡፡
3. ለሽልማት የሚቀርft ሥራዎች ባህላዊ ይዘታቸውን ሳይለቁ የኅብረተሰftን ባህል እየተጠቀሙ ኢኮኖሚያዊ አቅምን ለማሳደግ እንዲያስችሉ ሆነው ጥበባዊ ውበት፣ ማራኪነትና ሣቢነት ባለው ሁኔታ የቀረft መሆን ይገባቸዋል፡፡

## 6) ስለተወዳዳሪዎች አግባብነት

1. ማንኛውም የሽልማት መስፈርቱን የሚሟላ በዘርፉ የተሰማራ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ለወድድር መቅረብ ይችላል፡፡
2. የውድድሩ ተሳታፊዎች ቀደም ብለው በተሸለሙበት አንድ ዓይነት ሥራ በድጋሚ ለውድድር ሊቀርft አይችሉም፡፡

## 7) ሽልማት የሚሰጥባቸው የባህል ዘርፎች

1. ዕውቅናና የማበረታቻ ሽልማት የሚሰጥባቸው የባህል ኢንዱስትሪ ዘርፎች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-
   ሀ. ትዕይንታዊ ጥበባት
   ለ. ዕይታዊ ጥበባት
   ሐ. ዕደ ጥበባት
   መ. ሥነ-ፅሁፍ
2. ሚኒስቴሩ በያንዳንዱ የባህል ኢንዱስትሪ ዘርፍ ለሽልማት የሚያበቁ ዝርዝር መሥፈርቶችን ከማህበራትና ከክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች ጋር በጋራ ያወጣል፡፡

## 8) የሽልማቱ እና ዕውቅና አሰጣጥ ሥርዓት

1. ሽልማቱ የሙያ ብቃት ውድድሮች ላይ ተመስርቶ በዓመት አንድ ጊዜ በመጨረሻው ሩብ ዓመትዓብይ ኮሚቴ በሚወስነው ወርና ጊዜ ይከናወናል፡፡
2. አንድሥራ ለሽልማት የሚበቃው ለየዘርፉ የተዘረዘሩት የመመዘኛ መስፈርቶችንሲያሟላ እና በኮሚቴው የነጥብ አሰጣጥ ከሌሎች የላቀ ሆኖ ሲገኝ ይሆናል፡፡
3. የመመዘኛ ነጥቦችን በዘርፉ በተቋቋሙ ማህበራት ተዘጋጅተውበዓብይ ኮሚቴው የሚያጸድቁ ይሆናል፡፡
4. ማህበራት በየዘርፉ በሚወጣው መሥፈርት መሠረት ባለሙያዎችን በማወዳደር ያገኙትን ውጤት ለዓብይ ኮሚቴው ያቀርባሉ፡፡

## 9) ስለሽልማት

በሀገር አቀፍ ደረጃ አሸናፊ ለሚሆኑ የዘርፍ ተዋንያንየዕውቅናሽልማትይሰጣል፤ ዝርዝር አፈፃፀሙ በዓብይ ኮሚቴው የሚወሰን ይሆናል፡፡

# ክፍል ሶስት

## ኮሚቴ
## ስለማቋቋም

## 10) ዓብይ ኮሚቴ ስለማቋቋም

1. የሀገር አቀፍ የባህል ኢንዱስትሪዘርፍየሽልማት ሥርዓትንበዋናነት የሚመራ ዓብይ ኮሚቴ ከሚኒስቴር መ/ቤቱና ከሙያ ማህበራት ተውጣጥቶ ይቋቋማል፡፡
2. ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የዓብይ ኮሚቴውን ሰብሰቢ ይሰይማል፡፡
3. ዓብይኮሚቴው እንዳስፈላጊነቱ ንዑሳን ኮሚቴዎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

## 11) የኮሚቴው ስብሰባ

1. ኮሚቴው ስብሰባውን አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ሊያደርግ ይችላል፤
2. ከኮሚቴው አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፤
3. የኮሚቴው ውሳኔ በአብላጫ ድምፅ ይወሰናል፡፡ ድምፁ ለሁለት እኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፤
4. ኮሚቴው የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፤

## 12) የኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት

1. ስለሽልማት ሥነ-ሥርዓቱ አፈፃፀም ዝርዝር የሆነ እቅድና የድርጊት መርሐ ግብር ያዘጋጃል፤
2. ውድድሩ አግባብነትና ሚዛናዊነት ባለው መልኩና በተዘጋጁ መሥፈርቶች ላይ ተመሥርቶ መከናወኑ ይመዝናል፤
3. ከሚኒስቴር መ/ቤቱና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ይሠራል፤
4. ውድድሩተዓማኒ፤ አሳታፊ እና ፍትሀዊነቱን ጠብቆ እንዲካሄድ ይሠራል፤
5. ዕውቅና እና የሽልማትየመስጠት ሂደቱን በመገምገም ክፍተቶችን ለማስቀረት የሚያስችሉ ተግባር ያከናውናል፤
6. የሽልማቱን ሂደትና ዕድገት ለማህበራት በየጊዜው ያሳውቃል፤
7. ከማኅበራት ተዘጋጅቶ የመጣውን የውድድር መስፈርት ያፀድቃል፤

8. ለሥራው አጋዥ የሆኑ ንዑሳን ኮሚቴዎችን ይድግፋል ይከታተላል
9. የአሸናፊዎችን ስም ዝርዝር ከማህበራት ይሰበስባል፤ እስከ ሽልማቱ ቀንድረስ በሚስጥር ይጠብቃል፤
10. የሽልማቱንዓይነት ይወስናል፡፡

## 13) <u>የባህልሙያ ማህበራት ተግባርና ኃላፊነት</u>

1. የመወዳደሪያ መስፈርቱንና ሂደቱን በማዘጋጀት ለዓብይ ኮሚቴው አቅርበው ያፀድቃሉ፤
2. ውድድሩን በተቀመጠው መስፈርትእናሂደትበማከናወን ውጤቱን ለዓብይ ኮሚቴ ያሳውቃሉ፤
3. የዕውቅናእና የሽልማት አሰጣጥ መሠረታዊ መርሆዎችን ለማህበራቸው አባላት በመግለጽ ሰፊ ተሳትፎ እንዲፈጠር ያደርጋሉ፤
4. በውይይት እና በተግባር እንቅስቃሴ ወቅትከማህበራቱ የተወከሉ አባላት በንቃት እንዲንቀሳቀሱ ያደርጋሉ፤
5. ማህበሩን ለሚወክሉየዓብይም ሆነ የንዑሳን ኮሚቴአባላት አስፈላጊውን ድጋፍ ያድርጋሉ፤

## 14) <u>የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ተግባርናኃላፊነት</u>

1. ሀገር አቀፉ የሽልማት ሥነ-ሥርዓትን በበላይነት ይመራል፤
2. በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚሰጥ የሽልማት በጀትይመድባል፤ከዘርፍ ማህበራት ጋር በመሆንምተጨማሪ በጀት ያፈላልጋል
3. ከክልሎችና ከማህበራት ጋር በጥምረት ይሠራል፤ እንዲሁም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የፌዴራል መሥሪያ ቤቶች ትብብር ይጠይቃል፤
4. በሽልማት ሂደቱአፈፃፀም ላይ በቂ ተሳትፎና ክትትል ያደርጋል፤
5. የተሸላሚዎችን መረጃ ያደራጃል፤ያሰራጫል፤
6. የሽልማቱን ሂደት በመረጃዎች በማስደገፍ ለኅብረተሰfi ያሳውቃል፤
7. ክልሎችና ማህበራቱ የሚወያዩበትን እና የሽልማቱን አቅጣጫ የሚያስቀምጡበትን መድረክ ያመቻቻል
8. ሽልማቱን ለማስኬድና ሂደቱን እንዲመሩ የተቋቋሙ ኮሚቴዎችን ይደግፋል፤
9. ሰፊ የመገናኛ ብfiሀን ሽፋን ለመፍጠር እንዲቻል በልዩልዩ ስልቶች ከማህበራትና ከክልሎች ጋር ተቀናጅቶ ይሰራል፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ

15) **የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ይህን መመሪያ ሥራ ላይ በማዋል ረገድ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

16) **የቅሬታ አቀራረብ**

1. በማበረታቻ ሽልማት ሂደት እና አሰጣጥ ስርዓት ላይ ቅሬታ ያለው አካል የሽልማት ስርዓቱ በተከናወነ በ10 (አስር) ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለዓብይ ኮሚቴው በጽሑፍ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. ዓብይ ኮሚቴው በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ውሳኔውን በታወቀበ5 (አምሰት) ቀን ውስጥ ቅሬታውንለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ማቅረብ ይችላል፡፡

17) **ተፈፃሚነት ስለሌላቸው ህጎች**

ይህንን መመሪያ የሚቀረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በመመሪያው በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

18) **መመሪያውን ስለማሻሻል**

ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው መመሪያውን ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

19) **መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከፀደቀበት ሰኔ 4 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡